# ከተከባበርን ሁሉም ይቻላል

ለውድ አንባቢዎች

ከዝህ በፊትም ለዚህ ወብሳይት በመከፈቱ ደስታዬን ለመግለጽ አጭር ደብዳቤ ፅፌየ ነበር፡፡

እና አሁንም በድረ-ገፆች ያየሁት ሃሳቦች ይህን ፅሑፍ እንዳቀርብ አስገድዶኛል።

ልክ “ኢሮብ ማብሎ” ስሙ እንደምገልፀው የኢሮብ ሕዝብም ሌላም እውስጣቸው ያለውን ሓሳብ ላገራቸውና ለወንድሞቹም ለእህቶቹም ይበጃሉ ብሎው ካሰቡ ወደ ኋላ ማለት አያስፈልግም፡፡ እዚህ ላይ አንድ የራሱ እይታን ስገልፅ ልዩነትና አለመግባባት መፈጠሩ አይቀርም፡፡ዋናው ግን ይህን ሃሳብ በመቀራረብና በመቻቻል እንጂ ከእሮብ ባህል በወጡ ለዘብ ያላሉና ሃይለቃል በመጠቀም አይደለም፡፡

*“I must respect the opinions of others even if I disagree with them.” , Herbert Henry Lehman.*

ለዝህም ከአሁኑ ጀምረን ያባቶቻችና የአያቶቻችን ባህል የወረሰው የመከባበር ግንኙነት ይኑረን፡፡ “ ንመዐ ማራ ትታ ዓሲምኖይ ንኣባህ ኑቡሩህ ንፅንዳትያ ንናባትያ ንአቦብ ንእኖን ንቃይሲት ናስካባሮይ ”

ይቅርታ ይደረግልኝና ለዝህ እንደምሳሌ መግለጽ የምፈልገው መጀመርያ በብዕር ስም ባህልቢ ዘማርያም በሚል የተጠቀሱ ወንድማችን ፀሓፊ የኢሮብ ባህልን (ሱግሳክ ንቡር) መሰረት ያደረገ ሓላፊነትና ግልፅነት ያለው ሓሳብ እንድሁም ለሌሎች አርኣያ እንድሆኑ ስማቸው ግልፅ ብያደርጉ ችግር የለውም።

ሁለተኛ ደግሞ ለአንድ አብሮ በውጭ ለምኖር ወንድማችን እንድሁም ወንድሙን ለማቀራረብና ለውይይት የማይጋብዙ እንደ “ካድሬ” ና “ርካሽ ተንኮል” የመሰሉ ቃላቶችን ለማንም ለፀሃፊውም ቢሆን ለሰሚው የኢሮብ ሕዝብ ክብር የለውም፡፡

እዚህ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ሁሉም የብሔር ብሔረሰቦች ልዩነት ውበቱና ባህሉ ነው እየተባለ ነው። በልዩነታችን ከተባበርን ሁሉም ይቻላል እየተባለ ነው፡፡

ስለዝህ እኛም ማንም ማንንም ሳያገልልና ሳያስቀይም በመቀራረብ ውይይት ከተደረገ ሁሉም ይቻላል፡፡ ከግላችን በላይ ላገርና ለህዝብ ጥቅም ለምያስከበር ክብደት እንስጠው፡፡

ከሙሉ በየነ

ዓዲራት ኢትዮጵያ